Personal ID: 0506

# አገት

## የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

እኔም የዕርቅ ሀሳብ አለኝ

ሰኔ 2012 ዓም

ሀላባ

## አዘጋጅ

**ዩጎሬ ዳቆሮ ዲዶ**

**የሀላባ ዞን ጤና መምሪያ**

**ጁኒየር ፐብሊክ ሄልዝ ፕሮፌሺናል**

**በጂማ ዩኒቨርሲቲ Master of Public Health in General Public Health**

**የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ**

## አድራሻ

Email: yegoredakoro@gmail.com

yegoredakoro@students.ju.edu.et

Facebook: https://www.facebook.com/habib.dakoro

Telegram: https://t.me/HabibDakoro

Phone Number: +251913365294

Skype: https://join.skype.com/invite/BlllkoljDxud

Zoom PMI: 732 266 2737

Imo: https://call.imo.im/Habib_Dakoro

የቃላት መፍቻ ...... iii
ምስጋና ...... iv
መግቢያ ...... v
የሀላባ ብሔረሰብ ...... 1
የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት (ሴራ) ...... 1
የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ...... 2
ኦገቴ (ሸንጎ) ...... 3
ቦኪ/ሚኒ ኦገቲ ...... 3
ደቦ ኦገቲ ...... 4
ሀላቢ ኦገቲ ...... 4
ጎጎቲ ኦገቲ ...... 4
የኦገት ስርዓቶች (ሀሌ ሴረ) ...... 5
ቆርቶ ...... 5
ጉምጉማ ...... 6
ሎኮ ...... 6
ሙርቴ ...... 6
ፊጣ ...... 6
የግጭት አይነቶች ...... 6
የቅጣት አይነቶች ...... 7
ወርጃሙ ወደፊ ...... 7
ጉመ ...... 7
ጉደ ...... 8
ያዩ ...... 8
የኦገት ስርዓት እንድምታዎች ...... 8
የኦገት ወቅታዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አቅጣጫ ...... 9
ማጠቃለያ ...... 12
ዋቢ መፅሐፍት ...... 13
አባሪዎች ...... 14

## የቃላት መፍቻ

| | |
|---|---|
| ሴራ | አስተዳደር ስርዓት |
| ወማ | አለቃ |
| ቆርቶ | አፈ-ጉባዔ |
| ጉምጉማ | የድጋፍ ድምጽ |
| ሎኮ | አስተያየት |
| ኦገቴ | ሸንጎ |
| ሀላ | የዛፍ ጥላ/የኦገት መቀመጫ |
| ቦኮ/ሚኒ | ቤተሰብ |
| ደቦ | ጎሳ |
| ጎጎተ | ጠቅላይ ሸንጎ |
| ፊጠ | በዉሃ የተበጠበጠ ማር |
| ሩበት | ዋስ |
| ሙሪቹ | ተጠሪ |
| ዬየቀሙ | በላ ልበልሃ |
| ዱዱቡ | መረጃ |
| ኩዕላኑት | ከሳሾች |
| ሚሻላ | የሀላባ ባህላዊ መረዳዳት |
| ያደሀ | በይደር የቆየ አጀንዳ |
| ካያሀ | አዲስ አጀንዳ |
| ዞሁ/ቤቂሁ | የመኖሪያ ቀዬን ለቆ መኮብለል |

ማሳሰቢያ፡- እነዚህን ቃላት የሀላቢሳ ቋንቋ ድምጸት (Phenology) በተከተለ መንገድ አስፍሬአቸዋለሁ፡፡ ድምጸቱም ቃላቱን እንደተጠቀምኩበት ቦታ (Context) ይለያያል፡፡

## ምስጋና

ይህን ሰነድ በማዘጋጀት የብሔረሰቤን የዳበረ የግጭት አፈታት ስርዓት በሀገር ደረጃ ለማስተዋወቅ የሚያስችል ዕድል በማመቻቸቱ ‹‹ቲክቫ ኢትዮጵያን›› አመሰግናለሁ፡፡ በመቀጠል ዉድድሩ ላይ እንድሳተፍ መረጃ በማቀበል እና በማማከር ከጎኔ የነበሩትን የኢፌዴሪ ሰይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴዔታ የሆኑትን ዶ/ር ያንያ ሰይድ መኪ ለማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ባስተመጨረሻም በአርትኦት የረዳችኝ ባለቤቴን ወ/ሮ ኑሪቱ ናስር እንዲሁም በሰነድ ዝግጅቱ ወቅት የተለያዩ ዋቢ መጽሐፍትን በማቅረብ የተባበረኝን የስራ ባልደረባዬ አቶ ቃድሬ ጌትቻን እና ከጎኔ ሆነዉ የተባበሩኝና ያበረታቱኝን ጓደኞቼን አመሰግናለሁ፡፡

# መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ እየገጠማት ያለዉን ቀዉስ በሀገር በቀል መፍትሔ ለመፍታት እና ወደ ተሸላ ምዕራፍ ለማሻገር ብሎም ሰላምን ለማረጋገጥ ባህል ወሳኝ ነዉ፡፡ ሰላም የሁሉ ነገር መሰረት ነዉ፡ ፡ ሰላም ለሀገር ዘላቂነት፣ ለህዝቦች አብሮ መኖር እና ለሀገር ዕድገት ወሳኝ ነዉ፡፡ በህዝቦች አብሮነት መካከል ሰላም እንዳለ ሁሉ በተለያዩ አጋጣሚዎች ግጭቶች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህን ግጭቶች ሁሉም ማህበረሰብ በራሱ ባህላዊ ስርዓት እየፈታ እልፍ አመታትን በአብሮነት ዘልቋል፡ ፡ እነዚህን መልካም ባህላዊ እሴቶች ጠብቆ ለማቆየት በርካታ ተቋማት የሚሰሩ ስሆን ከነዚህም መካከል ‹‹ቲክቫ ኢትዮጵያ›› ‹‹እኤም የዕርቅ ሀሳብ አለኝ›› በሚል መርህ ቃል በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኙ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን ለማስተዋወቅ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ ፅሑፍ ‹‹ኦገት›› በሚል ርዕስ የሀላባን ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት እናቀርባለን፡፡ የሀላባ ባህል ሰፊ ጥናት የሚፈልጉ በርካታ እሴቶች ያሉት ቢሆንም በጥናትና ምርምር ዘርፍ እምብዛም ትኩረት ያላገኘ በመሆኑ ባህሉ በሰፊዉ ልተዋወቅ አልቻለም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በዘርፉ ጥናት ማድረግ የሚፈልጉ አካላት ባህሉን በማጥናት ያሉትን መልካም እሴቶች ለሀገር ሰላም ግንባታ እንድያዉሉት እጋብዛለሁ፡፡

## የሀላባ ብሔረሰብ

የሀላባ ዞን በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ስር ከሚገኙ 17 ዞኖች መካከል አንዱ ስሆን በሶስት የወረዳ እና በአንድ የከተማ አስተዳደሮች ተዋቅሮ ይገኛል፡፡ የዞኑ መቀመጫ ሀላባ ቁሊቶ ስሆን ከክልሉ ዋና ከተማ ሀዋሳ ባስተሰሜን ምዕራብ 87 ኪ.ሜ እንዲሁም ከአዲስ አበባ በስተደቡብ (በቡታጅራ) በኩል 245 ኪ.ሜ እንዲሁም (በሻሸመኔ) በኩል 315 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የዞኑ የቆዳ ስፋት 994.66 ኪ.ሜ$^2$ እንደሚሸፍን ይገለጻል (1)፡፡

ሀላባ በስተሰሜን ከስልጤ፣ በስተደቡብ እና በስተሰሜን ምዕራብ ከሀዲያ፣ በስተሰሜን ምስራቅ ከሻላ ሀይቅ፣ በስተምስራቅ ከኦሮሚያ ክልል እና በስተደቡብ ምዕራብ ከከንምባታ ጠምባሮ ዞኖች ጋር ያዋስናል፡፡ በ1999 ዓም በተካሄደዉ የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መሰረት የሀላባ ህዝብ ብዛት 232,325 ስሆን የህዝብ ጥግግቱም 233.76/ኪ.ሜ$^2$ እንደሆነ ይገለጻል (2)፡፡ ሀላባ ሞቃታማ እና በአብዘኛዉ ወይነደጋ የአየር ንብረት አለዉ፡፡ ከባህር ጠለል በላይ ከ1500-2396 ሜ ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ 857-1085 ሚሊ ስሆን የሙቀት መጠኑ 23-25 ድሴ እንደሚሆን ይገለጻል (1)፡፡

የሀላባ ብሔረሰብ ስረወ-ግንዱ ከአረቢያ ምድር መነሻዉን አድርጎ በዘመናት ሂደት አሁን ካለበት ቦታ ልሰፍር ችሏል፡፡ የሀላባ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ ባህል፣ ቋንቋ፣ የአስተዳደር ስርዓት (ሴራ) እና በርካታ መልካም እሴቶች ያሉት ብሔረሰብ ነዉ፡፡ የብሔረሰቡ ቋንቋ ሀላቢኛ (ሀላቢሳ) ስሆን ቋንቋዉ ከኩሽቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል (3,4)፡፡

የሀላባ ብሔረሰብ ከመነሻዉ አርብቶ አደር የነበረ ብሔረሰብ ስሆን ከ19ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በዋናነት በእርሻ ስራና በከፊል አርብቶ አደርነት የሚተዳደር ነዉ (3,4)፡፡ የሀላባ ብሔረሰብ ባሳለበተዉ የረዥም ጊዜ የአስተዳደር ስርዓት ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር በጉርብትና ብሎም በደም ተሳስሮ ለዘመናት በአብሮነት የኖረ ህዝብ ነዉ፡፡ በዉስጡም በርካታ ብሔረሰቦችን አቅፎ ያየዘ ሲሆን ሌሎች ብሔሮችን ሳይጨምር እስከ አርባ የሚጠጉ የብሔረሰቡ ጎሳዎች ይገኙበታል (4)፡፡

## የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት (ሴራ)

የሀላባ ብሔረሰብ ከትዉልድ ትዉልድ እየተሸጋገረ የመጣ የራሱ የሆነ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት አለዉ፡፡ ይህ የብሔረሰቡ ስርዓት በብሔረሰቡ ቋንቋ ማለትም በሀላቢሳ ሴራ ወይም ቦበኔ በመባል ይታወቃል፡፡ ሴራ የሚለዉ የሀላቢሳ ቃል ባህል፣ ወግ፣ ደንብ ወዘተ ተብሎ ይተረጎማል፡፡ የሀላባ

ሴራ የብሔረሰቡን ቋንቋ፣ ባህልና የአስተዳደር ስርዓትን ያጠቃልላል። የሀላባ ብሔረሰብ ለሚተዳደርበት ህግ ተገዢ ሆኖ ይኖራል (1፣4)።

በሀላባ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ስልጣን በየደረጃዉ የተከፋፈለ ነዉ። የአስተዳደር ስርዓቱ ከቤተሰብ የሚጀምር ስሆን ቤተሰብ ዉስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን የሚፈታዉና ሌሎችንም ባህላዊ ክንዋኔዎችን የሚመራዉ የቤተሰቡ መሪ ነዉ። ጉዳዩ ከአንድ ቤተሰብ በላይ የሆነ በሚሆንበት ወቅት ይህን ችግር መፍታት የሚያስችል የቅርብ ቤተዘመዶችን የሚያሰባስብ የአስተዳደር እርከን አለ። ይህም ‹‹ምኒ›› በመባል ይታወቃል። የቅርብ ቤተዘመድ (ምኒ) የራሱ መሪ ያለዉ ስሆን ይህም በብሔረሰቡ ቋንቋ ‹‹ቦኪ ሙሪቹ›› በመባል ይታወቃል። በሀላባ ብሔረሰብ ሌላኛዉ የአስተዳደር እርከን በርካታ ቤተዘመዶች የሚገኙበት የጎሳ አስተዳደር እርከን ስሆን በዚህም በተለያዩ ቤተዘመዶች (ምኒ) መካከል የሚከሰቱ ችግሮች ይታዩበታል (1፣4)።

በብሔረሰቡ ከፍተኛዉ የአስተዳደር እርከን ጠቅላላ ጉባዔ ወይም ሸንጎ ስሆን ይህም በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ሀላቢ ኦገት›› ተብሎ ይጠራል። ይህ የአስተዳደር እርከን በተለያዩ የብሔረሰቡ ጎሳዎች መካከል የሚከሰቱ ችግሮችን ጨምሮ ሀገራዊ ዉሳኔን በሚሹ ነገሮች ላይ ዉሳኔ ይሰጣል። ይህ ዉሳኔ በሀላባ ብሔረሰብ የመጨረሻዉ ዉሳኔ ይሆናል (1፣4)። የሀላባ ብሔረሰብ ከአጎራባች ህዝቦች ጋር የሚያገናኛዉ ሌላም የአስተዳደር እርከን አለ። ይህ ድንበር ተሸጋሪ ችግሮችን ለመፍታትና ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር ያለዉን ሰላማዊ እንቅስቃሴንና ትብብርን ለማጠናከር የሚረዳ የአስተዳደር እርከን ነዉ። ይህም ‹‹ጎጎት ኦገት›› ተብሎ ይጠራል።

በሀላባ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት አንድ ማዕከላዊ ስልጣን የለም። በየደረጃዉ የራሱ ስልጣን እና ኃላፊነት ያለዉ የአስተዳደር እርከን አለ። እነዚህ የአስተዳደር እርከኖች በስራቸዉ ያሉ ጉዳዮችን ከሀይማኖት አባቶች እና ከአካባቢዉ ታላለቅ አባቶች ጋር በመሆን የሚመሩ ስሆን ተልዕኮዎች እና ዉሳኔዎችም ይህንኑ ተዋረድ ጠብቀዉ ይሄዳሉ። ይህ ባህሪዉ ከዘመናዊዉ የ‹‹ፌዴራሊዝም›› የአስተዳደር ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል።

## የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት

የሀላባ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የግጭት አፈታት እና የዕርቅ ስርዓት አለዉ። በሀላባ ብሔረሰብ የወንጀል ድርጊት በፈጸመ ግለሰብ ላይ የጠፋተኝነት ዉሳኔ ከመተላለፉ በፊት ጥፋተኛዉ ግለሰብ ዋስ ይጠራል። ይህ ሂደት በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ሩበት›› ተብሎ ይጠራል። ይህ ዋስ (ሩበት) በማናቸዉም ጉዳዮች ጥፋተኛዉን በሚመለከት ኃላፊነት የሚወስድ ይሆናል። ይህ የሚደረገዉ

ወንጀል የፈጸመዉ አካል ቢያመልጥ፣ የተጣለበትን ቅጣት ባይቀበል ወይም ሌላም አይነት ሂደቱን የሚያዉኩ ድርጊቶችን በሚፈጽምበት ወቅት ዋሱ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ዋስ ሆኖ በወንጀለኛዉ የሚጠራዉ አካል ወንጀለኛዉ ይቀርበኛል፣ ይሆነኛል የሚለዉን ሰዉ በመሆኑ ይህን ሰዉ ለላመስቀጣት ሲል ማናቸዉንም የእርቅ ሂደቱን ልያደፈርሱ ከሚችሉ ተግባራት ይቆጠባል (3)፡፡

## ኦገቴ (ሸንጎ)

በሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ከፍተኛዉ የአስተዳደር እርከን ‹‹ኦገት›› ነዉ፡፡ ኦገቴ በብሔረሰቡ ቋንቋ ስሆን ስተረጎም ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ሸንጎ የሚል ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ይህ የአስተዳደር እርከን በየደረጃዉ የሚገኝ ስሆን በየደረጃዉ የሚገኙ አስተዳደራዊ ዉሳኔዎች የሚተላለፉበት፣ አዳዲስ መረጃዎች የሚለዋወጡበት (ዱዱቡ) እና የተወሰኑ ዉሳኔዎች አፈጻጸም የሚገመገምበት ነዉ፡፡ መቀመጫዉም የዛፍ ጥላ ስር ‹‹ሀላ›› ነዉ፡፡ ኦገት ላይ የሚሳተፉ አካላት የስብሰባዉ መሪ (ወማ/ዳኛ)፣ የስብሰባዉ አፈ-ጉበኤዎች (ቆርቶ አናከት)፣ ዋሶች (ሩበት)፣ ባለጉዳዮች (ኩዕላኑት)፣ የጎሳ ወይም የብተዘመድ መሪዎች (ሙሪቾዎች)፣ ወጣቶች እና ሌሎች ፍቃደኛ ተሳታፊዎችም ይሳተፉበታል፡፡

‹‹ሀላ›› የራሱ የሆነ አሰራር አለዉ፡፡ ይህን አሰራር የሚተላለፍ አካል ዋስ (ሩበት) እንዲጠራ ተደርጎ ቅጣቱን ያቀርባል፡፡ በኦገት (ሀላ) ስርዓት ለቅጣት ከሚዳርጉ ነገሮች መካከል ለምሣሌ ያህል፡- እድል ሳያገኙ መናገር፣ ሌሎችን መዝለፍ ወይም በኃይለ-ቃል መናገር፣ አካላዊ ጥቃት ለማድረስ መሞከር ይገኙበታል፡፡ በመንገድ የሚያልፍ ሰዉ እንኳን ሳይቀር በሀላ ህግ ተገዢ ይሆናል፡፡ መንገደኛ ሰዉ ከሚጠበቅበት ኃላፊነቶች መካከል አንዱ በሀላ አጠገብ በሚያልፍበት ወቅት ሰላምታ ማቅረብ እና ‹‹በደህና ነዉ የተሰባሰባችሁት?›› በማለት የመጠየቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ይህን ማድረግ ሳይችል ከቀረ ተጠርቶ እንዲቀርብ ተደርጎ ይቀጣል፡፡ ይህ ሀላባ ላይ ያለ ማንኛዉም አካል ይህን የሰላም እሴት የሆነዉን ባህሉን እንዲያዉቀዉ እና እንዲተዳደርበት ለማድረግ በማሰብ ነዉ፡፡ ይህም ከዘመናዊዉ የፍርድ ቤት የችሎት ስርዓቶች ጋር በሰፊዉ የሚመሳሰል ነዉ፡፡

## ቦኪ/ሚኒ ኦገቲ

በሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት ስብሰባ ከቤተሰብ እስከ ‹‹ሀላቢ ኦገት›› ይደርሳል፡፡ በሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ አስተዳደር ‹‹ቦኪ ኦገት›› (የቤተሰብ ሸንጎ) ዝቅተኛዉ የአስተዳደር እርከን ነዉ፡፡ ይህ የአስተዳደር እርከን ከቤተሰብ እስከ ንዑስ ጎሳ አባላትን የሚያካትት የአስተዳደር እርከን

ነዉ። ኃላፍትናዉም በንዑስ ጎሳ አባላት መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን የሚፈታና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚያቃልል ነዉ። ይህ የአስተዳደር እርከን በቤተዘመድ ዉስጥ የተቸገረ የሚረዳበት፣ የተጣላ የምታረቅበት፣ ያጠፋ የሚታረምበት፣ ሚሻላ እና ከጎሳ የሚሰጡ ተልዕኮዎችን ተጠሪ ሆኖ የሚያስፈጽም የአስተዳደር እርከን ነዉ (1፣4)።

## ደቦ ኦገቲ

‹‹ደቦ ኦገት›. በሀላባ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት መካከለኛ የአስተዳደር እርከን ስሆን በጎሳ ዉስጥ የሚገኙ ንዑሳን ጎሳዎችን አጠቃሎ የያዘና ሁሉንም የጎሳ አባላት አባል አድርጎ የሚይዝ የአስተዳደር እርከን ነዉ። የዚህ ሸንጎ ተግባራና ኃለፊነት በንዑስ ጎሳ ደረጃ ቀርበዉ ከንዑስ ጎሳ አቅም በላይ ወይም በይግባኝ የሚቀርብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን የሚፈታ ማህበራዊ ተቋም ነዉ። ይህ ተቋም በጎሳዉ ታላቅ ቤት መሪነት እና በተለያዩ ቁጥር ባላቸዉ ሙሪቾ ተብለዉ በሚታወቁ አስፈጻሚዎች የሚመራ ነዉ (1፣4።

## ሀላቢ ኦገቲ

በሀላባ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ከፍተኛ የአስተዳደር እርከን ‹‹ሀላቢ ኦገቴ›› ስሆን በሀላባ ዉስጥ የሚገኙ ሁሉንም ጎሳዎች አባል አድርጎ የሚንቀሳቀስ አደረጃጀት ነዉ። የዚህ አደረጃጀት ተግባር እና ኃላፊነት ሰፊ ነዉ። ብሔረሰቡን የተመለከቱ ህጎችን፣ መተዳደሪያ ደንቦችን እና ከአጎራባች ህዝቦች ጋር ልኖሩ የሚገቡ ግንኙነቶችን የመወሰን ስልጣን አለዉ። የ‹‹ሀላቢ ኦገት›› በጎሳ ደረጃ ያልተፈቱና በይግባኝ መልክ የሚቀርቡ ግጭቶችን የሚፈታ ተቋም ነዉ። በሀላቢ ኦገት የሚወሰኑ ማንኛዉም ዉሳኔዎች ይግባኝ ስለሌላቸዉ በማንኛዉም መልኩ ተፈጻሚ ይደረጋሉ። የሀላባ ሴራ ተፈጻሚ የሚሆንበት ባህላዊ ችሎት የሚመራዉ ተቀባይነት ባላቸዉ ዋና ዳኞች ስሆን ተጠሪነቱ ለወማ ነዉ። ወማ የሚሰየመዉ የራሱ የሆነ ስርዓት ስኖረዉ የሚመረጠዉም ከሲዴ ጎሳ ነዉ (1፣4)።

## ጎጎቲ ኦገቲ

‹‹ጎጎቲ ኦገት›› ሀላባ ዉስጥ ከሚደረጉ የኦገት አይነቶች አንዱ ስሆን ይህ ኦገት ሀላባን ከአጎራባች ብሔረሰቦች ጋር የሚያስተሳስር የኦገት አይነት ነዉ። በዚህ ጠቅላላ ሸንጎ ላይ ከሀላባ አጎራባች ህዝቦች ከአርሲ፣ ሀዲያ፣ ስልጤ፣ ከምባታ እና ሌሎች ብሔሮች ጋር በጋራ መድረክ ይቀመጣል፡ ፡ በዚህም የድንበር ጉዳዮችንና የድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎችን፣ የጋራ ሀብትን በሚመለከትና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ከጋራ ስምምነት የሚደረስበት ነዉ።

## የኦገት ስርዓቶች (ሀሌ ሴረ)

ኦገት በርካታ የሆኑ ስርዓቶች አሉት፡፡ ስርዓቱ የሚካሄደዉ የዛፍ ጥላ ስር ስሆን አዘጋጆቹም እንደ ጉዳዩ (የኦገት አጀንዳ) እና የኦገት አይነት ይወሰናል፡፡ ኦገቴዉ በበዳይ ተበዳይ መካከል ያለን ጉዳይ ለመዳኘት የሚቀመጥ ከሆነ ኦገቴዉን ጥላ ማዘጋጀት የበዳዩ ይሆናል፡፡ ከዚህ ዉጪ ከሆነ ግን አንድ አካባቢ ተመርጦ በጋራ እንዲያዘጋጁ ኃላፊነት ይሰጣል፡፡ የኦገቴ ስርዓት የሚጀመረዉ በ‹‹ዱዱቡ›› ነዉ፡፡ በኦገት ስብስብ ላይ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሰዎች ስለምሳተፉ በየአካባቢዉ ያለን አዲስ መረጃ በመለዋወጥ ይጀመራል፡፡ በመቀጠልም የዕለቱ አጀንዳ ይቀመጣል፡ ፡ ይህንንም ቆርቶዎች በይደር የቆየ ነዉ ወይስ አዲስ አጀንዳ ነዉ በማለት በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ያዳህንዶ ካያሀ?›› በማለት ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ መልኩ አዲስም ይሁን በይደር የቆየ አጀንዳ ለቤቱ በማሳወቅ መድረኩን ያስጀምራሉ (1፣4)፡፡

ከዚህ በመቀጠል በተነሳዉ ጉዳይ መነሻ ‹‹በላ … ልበልሃ›› በሚል ስርዓት አመልካች ያቀረበዉን ክስ ያዳምጣሉ፡፡ ይህም በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ዬየቀሙ›› (ዬአ … የኖረዕኑ) ይባላል፡፡ በዚህ መሰረት ጥፋተኛዉን ጥፋቱን በማሳየት እንድያምን ይደረጋል፡፡ ጥፋተኛዉ ጥፋቱን የማያምን ከሆነ የዐይን እማኞች ካሉ እንዲመሰክሩ ይደረጋል፡፡ የዓይን እማኝ ከሌለ ግን ከቤተሰቡ ታላቅ የሆነዉ ሰዉ ተመርጦ እንዲመክረዉ እና እንዲያሳምነዉ ይደረጋል፡፡ በዚህ መልኩም ማመን ካልቻለ ግን በእምነቱ መሰረት እንዲምል ይደረግና ጉዳዩ በምርቃት ይዘጋል፡፡ ጥፋተኛዉ ጥፋቱን ካመነ ግን ዋስ ‹‹ሩበት›› እንዲጠራ ተደርጎ ቅጣቱን እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ ቅጣቱ እንደ ወንጀሉ አይነትና መጠን ይወሰናል፡፡ የቅጣት ዉሳኔዉ በመድረኩ በተገኘ ሰዉ የድምፅ ብልጫ (ጉምጉማ) የሚወሰን ነዉ፡፡ ባስተመጨረሻም የዉይይቱ መሪ (ዳኛ) ስያጸድቀዉ ተፈጻሚ ይሆናል (1፣4)፡፡

## ቆርቶ

ቆርቶ በሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ዉስጥ ኦገትን በአፈ-ጉባኤነት የሚመሩ አካላት ናቸዉ፡፡ ቆርቶዎች በቁጥር ሁለት ስሆኑ የፍርድ እና የክርክር ሂደቱን ይመራሉ (1)፡፡ ቆርቶዎች የሀላባን ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ህጎችን ጠንቅቀዉ የሚረዱ እና የመሃል ዳኛ በመሆን ስሞታዎችን በማድመጥ እና የመከላከያ ቃል በመስማት ያከራክራሉ፡፡ ባስተመጨረሻም ጥፋተኛዉን ከለዩ በኂላ ዋስ (ሩበት) እንዲጠራ ያደርጋሉ፡፡ የጥፋተኝነት ዉሳኔ እና የቅጣት ዉሳኔን ከማስተላለፋቸዉ በፊት ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦችን በመያዝ ‹‹ጉምጉማ›› በሚባለዉ የሸንጎ ስርዓት የሌሎች የችሎቱ ታዳሚያን አስተያየት ያደምጣሉ፡፡ ባስተመጨረሻም አብዛኸኛዉ ታዳሚ የደገፈዉ ሀሳብ ለመጨረሻ ዉሳኔ ይቀርባል፡፡

### ጉምጉማ

ከሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት (ኦገት) ተግባራት ዉስጥ አንዱ ‹‹ጉምጉማ›› ነዉ፡፡ ጉምጉማ ማለት የኦገቴዉ ቆርቶዎች ጥፋተኛዉ ከተለየ በኂላ የቅጣት ዉሳኔ ላይ ከሸንጎዉ ተሳታፊዎች መካከል አስተያየት የሚቀበሉበት ስርዓት ነዉ (1)፡፡ በዚህ ስርዓት የክርክር ሂደቱን የተከታተለ ማንኛዉም አካል አስተያየት ይሰጣል፡፡ አስተያየት ሰጪዎቹ ቆርቶዎች (አፈጉባዔዎቹ) በሚያቀርቡት የቅጣት ዉሳኔ መነሻ ለሚደግፉት የቅጣት አይነት እና መጠን ድምጽ ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ስርዓት ጉምጉማ የማይፈቀድላቸዉ አካላት አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ባለጉዳዮች (ከሳሽ እና ተከሳሽ) እና የተከሳሽ ዋስ ይገኙበታል፡፡ ይህም ስርዓቱ ከአድሎኣዊነት እንዲጸዳ እና ሁለቱንም ወገን የሚያረካ ዉሳኔ ላይ ለመድረስ እንዲያስችል ነዉ፡፡ ይህ ባህሪዉ ኦገትን ‹‹አሳታፊነትና ግልጸኝነት›› ከሚባለዉ ከዘመናዊዉ የዴሞክራሲ መርህ ጋር ያመሳስለዋል፡፡

### ሎኮ

ሎኮ የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ‹‹ኦገት›› አንዱ አካል ስሆን ቆርቶዎች የሴራዉን ስርዓት ስስቱ ወይም ቆርቶዎቹ ከያዙት አቅጣጫ የተሻለ ሀሳብ አለኝ የሚል የኦገቴዉ ተሳታፊ አስተያየት የሚሰጥበት መንገድ ነዉ፡፡ አንድ ሰዉ በየትኛዉም ጊዜ ‹‹ሎኮ›› ብሎ የመድረኩን መሪዎች በሚጠይቅበት ወቅት እድል ይሰጠዋል፡፡ የሚያቀርበዉ ሀሳብ ተገቢ እና የተሻለ ሆኖ ከተገኘ ይቀበሉታል፡፡ ሀሳቡ የተሻለ ሆኖ ካልተገኘ ግን ዉድቅ ይደረጋል (1)፡፡

### ሙርቴ

ሙርቴ ዉሳኔ ስሆን አንድ ሰዉ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ በኂላ በጉምጉማዉ በተሰበሰበ ድምጽ መነሻ አብላጫዉ ጉምጉማ የደገፈዉ ቅጣት ይወሰናል፡፡ ይህም ተፈጻሚ የሚሆነዉ የኦገቴዉ መሪ (ወማ/ሙሪቹ) ስያጸና ነዉ (4)፡፡

### ፊጣ

ፊጣ ማለት በዉሃ የተበጠበጠ ማር ስሆን ከባድ ግጭቶች ተከስተዉ ሂደቱን ጠብቆ ስጠናቀቅ እና እርቅ ስፈጸም በጥፋተኛዉ በኩል ቀርቦ ኦገት በተቀመጠዉ ጥላ ስር በሙሉ ይረጫል፡፡ ይህም በዳይ እና ተበዳይ ፍቅራቸዉ ዳግም እንዲጣፍጥ የሚል ምኞት ለመግለጽ ነዉ፡፡

## የግጭት አይነቶች

ቀላል ግጭት፡- ይህ በተለያዩ ግለሰቦች መካከል፣ በቤተሰብ ደረጃ እና በጎረቤታሞች መካከል በዕለት ተዕለት ህይወት ልያጋጥሙ የሚችሉ ከቃል ያልዘለሉ ቅያሜዎች ስሆኑ በአብዘኸኛዉ ወደ ክስ

ደረጃ የማይደርሱ እና በዕርቅ የሚፈጸሙ ናቸዉ፡፡ እንደዚህ አይነት ግጭቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ጉዳዩ ላይ ዉይይት ከተደረገ በኂላ ሁለቱም ወገን ይቅር ይባባላሉ፡፡ ይህም ስርዓት ‹‹አፈዉቱ ሊላህ›› (ለአላህ ብሎ ይቅር መባባል) ተብሎ ይጠራል፡፡

መካከለኛ ግጭት፡- ይህ የግጭት አይነት በጎረቤታሞች፣ በጎሳዎች መካከል እና ከአጎራባች ህዝቦች ጋር የሚደረግ ደም አልባ እና የንብረት ዉድመት ያሌለበት የግጭት አይነት ነዉ፡፡ እነዚህ ግጭቶች ባህላዊዉን የግጭት አፈታት ሂደት የሚከተሉ ይሆናሉ፡፡

ከባድ ግጭት፡- ይህ የግጭት አይነት የደም ማፍሰስ፣ የአካል መጉደል፣ የነፍስ ማጥፋት፣ አስገድዶ መድፈር፣ ከባድ የንብረት ዉድመት፣ ስርቆትና ዘረፋ፣ የሀገር ክህደት እና ክብር እና ማንነትን ማዋረድን ያካትታል፡፡ ይህ የግጭት አይነት ከፍተኛ ፍርድ የሚፈልግ እና ከፍተኛ ቅጣት የሚያስጥል የጥፋት አይነት ነዉ፡፡

# የቅጣት አይነቶች

## ወርጃሙ ወደፈ

ወርጃሙ በጥሬ ትርጉሙ ኮርማ ማለት ነዉ፡፡ ይህ ቅጣት በሀላባ ብሔረሰብ በሰፊዉ የሚተገበር የቅጣት አይነት ስሆን የሚቀርበዉም ለ‹‹ሀላዉ›› (ኦገት ተሳታፊዎች) ነዉ፡፡ ወርጃሙ የሳር እና የቅጠል ተብሎ በሁለት ይካፈላል፡፡ ይህ የሚወሰነዉ እንደ ጥፋቱ ክብደት ስሆን ወንጀሉ ከፍ ያለ ስሆን የሳር (የከብት ኮርማ) ይወሰናል፡፡ ጥፋቱ ከዚያ ያነሰ ስሆን የቅጠል (ቀንጣቢዎች በግ/ፍየል) ይወሰናል፡፡ ወርጃሙ በገንዘብ ተተምኖም ልቀርብ ይችላል፡፡  ለኦገት የሚቀርበዉ ኮርማ ወይም በግና ፍየል እዚያዉ ይታረዳል፡፡ በኦገቱ ያለ ማንኛዉም አካል ከእርዱ ይበላና ጥፋተኛዉን ይመርቃል፡፡ ነገር ግን የቀረበዉ ወርጃሙ በገንዘብ ተተምኖ ከሆነ ለሁሉም ይከፋፈላል (1፣4)፡፡

ወደፈ፡ ከወርጃሙ በተጨማሪ የሚጣል ቅጣት ነዉ፡፡ ይህ የቅጣት አይነት የሚወሰነዉ ጥፋቱ የተሰራበት ሰዉ ከጥፋተኛዉ ልዩ ክብር የሚገባዉ ከሆነ  ነዉ፡፡ ለምሳሌ ወላጆች፣ ታላቅ ወንድም እና አማች በሚሆንበት ወቅት ከወርጃሞ በተጨማሪ ወደፋ እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ ለወደፋ የሚቀርበዉ ማር ስሆን በማይገኝበት ወቅት ግን በገንዘብ ተተምኖ ልቀርብ ይችላል፡፡

### ጉመ

ጉመ በሀላባ ባህል ከከፍተኛ የቅጣት አይነቶች አንዱ ነዉ፡፡ ጉመ ማለት ካሳ ማለት ስሆን ታስቦበት ለተፈጸመ የነፍስ ግድያ፣ የአይን መጥፋት እና የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች ጥፋተኛዉ የሚያቀርበዉ የቅጣት አይነት ነዉ፡፡ ጉመ የሚከፈለዉ በከብት ስሆን ብዛቱም እንደ ጥፋቱ አይነት

እስከ አንድ መቶ ግደር ልደርስ ይችላል። ለጉማ የሚቀርብ የከብት አይነት ግደር ቢቻ ስሆን ይህም ግደሮቹ ደርሰዉ በሚወልዱበት ወቅት ተጎጂዉን ወይም የተጎጂዉን ቤተሰብ እርም ያወጣሉ ተብሎ ስለምታሰብ ነዉ። ይህን ቅጣት ጥፋተኛዉ መክፈል የማይችል ከሆነ ግን በእናት እና በአባት በኩል ያሉ የቅርብ ቤተዘመዶችን ጨምሮ ጎሳዉ ኃብት በማሰባሰብ ይረዳዋል (4)።

## ጉደ

ጉደ የሚባለዉ የቅጣት አይነት በድንገት (ሳይታሰብ) ለሚከሰት የነፍስ መጥፋት ወንጀል የሚወሰን ቅጣት ስሆን ግጭቶችን ለማብረድ እና ቂም በቀልን ለማስቀረት የሚደረግ የጥቁር እርድ ነዉ። በዚህ የቅጣት ሂደት የሟች ቤተሰብ ገዳይን ይቅር በማለት የሚመርቁበትና የምታረቁበት ነዉ (4)።

## ያዩ

ይህ የቅጣት አይነት በሀላባ ባህል ከሚጣሉ ከፍተኛ የቅጣት አይነቶች የሚመደብ ነዉ። ቅጣቱ የሚጣለዉ በሀላባ ዉስጥ የሚኖር ሆኖ በሀላባ ሴራ መሰረት የተበየነበትን ዉሳኔ አሻፈረኝ በማለት ሳይቀበል ስቀር ነዉ። ቅጣቱ ማህበረሰባዊ ማግለል ስሆን የጥፋተኛዉ ቤተሰብ ከማናቸዉም ማህበራዊ ግንኙነቶች እንድቋረጥ ይደረጋል። ከለቅሶ፣ ከሠርግ፣ ከማህበራዊ አገልግሎት ጭምር ይገለላል። እርዳታ ቢጠይቅም አያገኝም። ይህ ቅጣት የሚዘልቀዉ ጥፋተኛዉ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ በመጠየቅ የተጣለበትን ቅጣት ተቀብሎ እስኪከፍል እና ለሴራ ተገዥ እስኪሆን ቢቻ ነዉ (1፣4)።

# የኦገት ስርዓት እንድምታዎች

የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት በርካታ እሴቶች እና ትሩፋቶች አሉት። እነዚህ እሴቶች እና ትሩፋቶች የሀገሪቱን አሁናዊ ሁኔታ ከማሻሻል አንጻር ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላሉ። በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ በዋናነት የሚስተዋሉት የግጭት አይነቶች ብሔርን መሰረት ያደረጉ፣ ሀይመኖትን መሰረት ያደረጉ እና ድንገተኛ አደጋዎች ናቸዉ። እነዚህ ሶስቱም የግጭት አይነቶች ሀላባ ላይ ተከስተዉ በባህላዊ ስርዓቱ ተፈተዋል። ለምሳሌ ያህል በ2000/2001 ዓም ተከስቶ የነበረዉ የሀላባ እና የአርሲ ብሔረሰቦች ግጭት የነፍስ መጥፋት እና የንብረት ዉድመት ያደረሰ ስሆን በሴራዉ መሰረት በጉዳ አልቆ እርቅ ተፈጽሟል። በ2006 ዓም በደረሰ የመኪና አደጋ አራት የአንድ ቤተሰብ አባላት ህይወታቸዉ በማለፉ በሴራዉ መሰረት በጉማ እርቅ ተፈጽሟል። በቅርቡ በ2011ዓም በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ቤተ-እምነቶች ላይ የደረሰ

ጉዳትም እንዲሁ ምንም አይነት የሰዉ ህይወት ሳይጠፋና ጉዳዩ ወደ ከፋ ግጭት ሳያመራ በሴራዉ መሰረት ሊያልቅ ችሏል፡፡

በሀላባ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ግጭትን ለማብረድ ስባል የሚሰሩ በርካታ ተግባራት አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በድንገትም ይሁን ታስቦበት የሰዉ ነፍስ በሚጠፋበት ወቅት ሽማግሌዎች መረጃዉ እንደደረሳቸዉ ወደ ገዳይ ቤት በማምራት ሰዉን እና ነፍስ ያላቸዉን እንሰሳት ከቤት በማራቅ ቤቱን ከዉጪ በመዝጋት በእሾህ ያጥራሉ፡፡ ይህም በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ዞሁ/ቤቁሁ›› ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ተግባር የሚፈጸመዉ በሽማግሌዎች ወይም በገዳዩ ቤተሰብ ስሆን ዓላማዉም በሟች ቤተሰብ በኩል ልደርስ የሚችልን የበቀል እርምጃ ለመከላከልና ጉዳዩ ሳይባባስ ለማብረድ ነዉ፡፡ የሟች ቤተሰብ የተዘጋ ቤት በሚደርስበት ወቅት በሴራዉ እርምጃ መዉሰድ የሚከለከል በመሆኑ ከድርጊቱ ይታቀባል፡፡ በመቀጠልም ሽምግልና ተወስዶ በጉዳ ወይም በጉማ ጉዳዩ እንድያልቅ ይደረጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሁለት ወገን በሚጋጭበት ወቅት የደረሰ ሶስተኛ ሰዉ የመለያየት አቅም እንኳን ባይኖረዉ በእጁ የያዘዉን ነገር መሬት ላይ በመጣል ‹‹እኔን ደብድቡኝ›› ካለ ሁለቱም ወገን ፀቡን ያቆማል፤ ሌላዉ ሁለት የተለየዩ ጎሳዎች በሚጋጩበት ወቅት የአንዱ ወገን ቢደርስ ቀድሞ እርምጃ የሚወስደዉ የራሱ ወገን ላይ ነዉ፡፡ ያኔ ተቃራኒዉ ወገንም ከእርምጃዉ ይታቀብና ጉዳዩ ወደ ሽምግልና ስርዓት ይገባል፡፡ ከዚህ ላይ ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓቶች ህብረተሰቡ ዘንድ ታዓማኒ እና ተሰሚነት ያላቸዉ መሆናቸዉንና ከቂም እና ቁርሾ በመጽዳት ሰላምን በጽኑ መሰረት ላይ እንዲቆም ማድረግ የሚችሉ መሆናቸዉን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## የኦገት ወቅታዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አቅጣጫ

የሀላባ ብሔረሰብ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት (ኦገት) በኢትዮጵያ የተመሰረተዉን ዘመናዊዉን ስርዓተ-መንግስት አወቃቀር ተከትሎ በየጊዜዉ ሚናዉ እየተቀየረ ቆይቷል፡፡ በቀደመዉ ጊዜ ኦገቱ በሀላባ ብቸኛዉ አገልግሎት ላይ የመሚዉል የግጭት አፈታት ስርዓት ነበር፡፡ ይህም የሆነዉ በቀድሞዉ ጊዜ ሀላባ የራሱ ሀገረ መንግስት ስለነበረዉ ነዉ፡፡ ሀላባ የራሱ ሀገረ መንግስት ፈርሶ ኢትዮጵያ የዘማናዊዉን የአስተዳደር ስርዓት መከተል ከጀመረች ጀምሮ የሀገሪቱ የስርዓተ መንግስት አወቃቀር እስከ ታች ድረስ በመዝለቅ በየካባቢዉ የሚፈጠሩ ችግሮችን የሚፈታበት አቅም ስላልነበረ እና የነበረዉም ስርዓት በዋናነት ባህላዊዉን የአስተዳደር ስርዓት የሚከተል በመሆኑ ነበር (4)፡፡

ከደርግ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ግን ይህ እየተቀየረ መጥቷል፡፡ ከዚህ ቀደም እንደነበረዉ ብቸኛዉ የግጭት መፍቻ መንገድ መሆኑ ቀርቶ በአካቢበዉ ከሚገኙ ዋና ዋና የግጭት መፍቻ መንገዶች መካከል አንዱ ልሆን ችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት ሀላባ ዉስጥ ሶስት አይነት የግጭት መፍቻ መንገዶች አሉ፡፡ እነዚህም ዘመናዊዉ የህግ ስርዓት (ፍርድ ቤቶች)፣ የሸርዓ ፍርድ ቤቶች እና ኦገት ናቸዉ፡፡ እነዚህ ሶስቱም አማራጮች ለተበዳዩ በቅርበት የቀረቡ ስሆን በሚፈልገዉ ስርዓት የመዳኘት መብቱ የተከበረ ነዉ፡፡

በአሁኑ ወቅት ኦገቴ ዘመናዊዉን የህግ ስርዓት በበጎ ጎን የሚያግዝ ስሆን ጉዳዮችን ከፍርድ ቤት በመዉሰድ በሴራዉ መሰረት እየፈታም ይገኛል፡፡ ይሁንና ብዝሃ ምርጫ መኖሩና በአሁን ወቀት አንዳንድ የቅጣት ዉሳኔዎች ከዘመናዊዉ የህግ ስርዓት ጋር የማይስማሙ በመሆኑ ተፈጻሚነታቸዉ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ ከነዚህ ተፈጻሚነታቸዉ ከቀሩ ባህላዊ የቅጣት አይነቶች መካከል አንዱ ያዩ (ማህበረሰባዊ ማግለል) ነዉ (4)፡፡ ምንም እንኳን ዓላማዉ ጥፋተኛዉን ለሴራዉ ተገዢ እንዲሆን ማድረግ ቢሆንም ከሰብዓዊ መብት አንጻር ግን ገደብ የሚጣልበት ሆኗል፡፡ ይህም ሆኖ ግን አሁንም በሰፊዉ የሚተገበር ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ነዉ፡፡ በተለይ ዳኝነቱ ቂምን እና ቅያሜን ከስሩ የሚያጸዳ በመሆኑ ዳግም በቂም በቀል የሚከሰት ግጭት አይኖርም፡፡ ኦገት ማንኛዉም መሳተፍ የሚፈልግ አካል የሚሳተፍበት በመሆኑ ወጣቶችን ጨምሮ በርካታ ሰዎች ይታደሙበታል፡፡ በዚህ መልኩ ወጣቶችን በማሳተፍ ቀጣዩ ትዉልድ ስርዓቱን እንዲለምድ እና ባህሉን እንዲረከብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ይህ የአስተዳደር ስርዓት ልክ እንደ ሌላዉ የህብረተሰብ ክፍል ወጣቱም ዘንድ ተቀባይነት አለዉ፡ ፡ የሚወሰኑት ዉሳኔዎችም በወጣቱ ላይ ጭምር ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ ስርዓቱ የወጣቶችን ሰብዕና ከመቅረጽ አንጻርም ጉልህ ድርሻ አለዉ፡፡ ነገር ግን ይህን የአስተዳደር ስርዓት ለወጣቱ ትዉልድ እንዲሸጋገር የሚሰራዉ ስራ በቂ አይደለም፡፡ እንደ ሀላባ ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት ወጣቶች በየአካባቢዉ በሚከሰቱ ጉዳዮች ላይ በሚፈጠሩ ኦገት ላይ በመሳታፍ እና ከታላላቆች በመጠየቅ ከሚያገኙት እዉቀት ባሻገር ባህሉን ጠብቆ ለማቆየት የሚያስችል ስራ ደካማ ነዉ፡፡ ባህሉ በትምህርት ካሪኩለም አልተካተተም፣ በመፅሐፍ ደረጃ በብዛት ታትሞ ተደራሽ አልተደረገም፣ የባህል ሲምፖዝየሞች በብዛት ተደራሽ አይደሉም፣ የሚድያ ሽፋኑም ቢሆን ለሁሉ ተደራሽ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንዳንድ የባህሉ ስርዓቶች ከዘመናዊዉ የፍርድ ስርዓት ጋር ያላቸዉ ግንኙነት እና አብሮ ማስኬድ በሚቻልባቸዉ መንገዶች ላይ የተሰራ ስራ የለም፡፡ ባህሉ አሁን ያለበት ሁኔታ እና ከወጣቱ አንጻር ያሉ ተግዳሮቶች አልተጠኑም፡፡

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን ለመፍታት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በባህል ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማት ወቅታዊ ጥናቶችን በማቅረብ በጥናት ላይ የተመሰረተ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የባህል ሲምፖዝየሞችን፣ ስልጠናዎችን፣ የሚድያ ሽፋን፣ የህትመት ስራ እና የኪነ ጥበብ ዉጤቶችን በመጠቀም ባህሉ ወጣቶች ዘንድ እንዲደርስ መስራት ያስፈልጋል፡ ፡ባህሎችን ለማስተዋወቅ ከሚረዱ ነገሮች አንዱ መሰል ፕሮጀክቶች በመሆናቸዉ መንግስትና ሌሎች የሚመለከታቸዉ አካላት እላይ በአንድ ማዕከል ቢቻ ሳይሆን መንግስት ባለዉ የባህልና ቱሪዝም እንዲሁም የሰላም እና ፀጥታ ሴክተሮች አማካይነት ለጉዳዩ ተኩረት በመስጠት ባህሎቹ ለሀገር ሰላም እና ለህዝቦች አብሮነት የሚያበረክቱትን ሚና ለማሳደግ መስራት ይኖርበታል፡፡

## ማጠቃለያ

በሀገራችን በርካታ ብሔረሰቦች የየራሳቸዉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች አሏቸዉ። እነዚህ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶች የማህበረሰቡን ሰላምና ደህንነት አስጠብቀዉ ለዘመናት አቆይተዋል። የሀላባ ብሔረሰብም በሴራዉ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያለዉ ስሆን የብሔረሰቡንና ብሔረሰቡ ከሌሎች አጎራባች ህዝቦች ጋር ያለዉን መስተጋብር ጠብቆ እንዲያቆይ ያስቻለ ታላቅ የሀገር ሀብት ነዉ። በመሆኑም በቀጣይ በባህል እና ቋንቋ ጥናት ላይ የሚሰሩ ተቋማት ይህን ባህል በማጥናትና ለሀገር ሰላም ግንባታ በማዋል በሀገር በቀል መፍትሔ ሀገራችን እየገጠማት ያለዉን ቀዉስ እንዲትሻገር የበኩላቸዉን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## ዋቢ መፅሐፍት


1. Culture and Ethno-History of Halaba. SNNPR Bureau of Culture and Tourism. Teddy Printing, June 2014, Hawassa.
2. CSA census report 2007. AA.
3. Halabissa Grammar Phenology, Morphology and Syntax. Fekede M. Council of Nationalities. Bole Printing Enterprise Aug, 2012. AA.
4. የሀላባ ብሔረሰብ ባህልና ታሪክ. ኤፍሬም ዘለቀ. የሀላባ ህዝብ ልማት ማህበር. ሮቦት ማተሚያ ቤት 2007 ሀዋሳ
5. Southern Nation Nationalities and People's Regional State Council of Nationalities: Strategy for Conflict Resolution and its Implementation Manual. December 2014. Hawassa

## አባሪዎች

ምስል፡ 1 የሀላባ ዞን አስተዳደራዊ ወሰን የሚያሳይ ካርታ




Map 2: Administrative Map of Halaba Special Woreda፡ the map does not include the three kebles which joined the Special Woreda recently (Source: SNNPR Bureau of Finance and Economic Development, 2005 E.C).

ምስል፡ 2 የሀላባ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት (ኦገት)



Fig.1: Ogate Halla (Photo, HWCTO, 2006 E. C, Kulito)

ምስል፡ 3 የሀላባ ብሔረሰብ የህግ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ አደረጃጀት መዋቅር




Fig 2: The Halaba Judico- Socio- Political Structure